ትናንሽ ተደርገው የሚታዩ ወንጀሎችን ተጠንቀቁ!

ከሰህል ቢን ሰዕድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: «የአሏህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል፡ "ትናንሽ ተደርገው የሚታዩ ወንጀሎችን ተጠንቀቁ! የትናንሽ
ወንጀሎች ምሳሌ ወደ አንድ ሸለቆ እንደወረዱ ሰዎች ምሳሌ ነው። ይሄም አንድ እንጨት ይዞ ሲመጣ፤ ያም አንድ እንጨት ይዞ ሲመጣ
ምግባቸውን (አቀጣጥለው) መጋገር እንደቻሉ ሰዎች ነው። ትናንሽ ወንጀሎች (የሚሰራውን) ባለቤት ባስያዙት ጊዜ መጥፊያው ይሆናሉ።"» [ሶሒሕ ነው።] [አሕመድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ትናንሽ ተደርገው የሚታዩ ወንጀሎችን መስራት ላይ ከመዘናጋትና አብዝቶ ከመስራት አስጠነቀቁ። ትናንሽ ወንጀሎች ተሰባስበው ባለቤቱን ያጠፋሉና። ለዚህም ወደ ሸለቆ ውስጥ የወረዱ ሰዎችን ምሳሌ አደረጉ። ሁሉም ያመጧቸው ትናንሽ እንጨቶች ተጠራቅመው ዳቦዋቸውን ለመጋገር እስኪያስችሏቸው ድረስ እያንዳንዳቸው ትናንሽ እንጨት ይዘው መጡ። ትናንሽ ወንጀሎችም ሰውዬው ሳይቶብት ወይም ከነርሱ አላህ ይቅር ሳይለው በነርሱ ምክንያት የተያዘ ጊዜ ያወድሙታል።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/66224